# ‘ሀገራችን ቀውስ ውስጥ ለምን ገባች?’

**ፀጋዝአብ ለምለም ተስፋይ**

**የኢኮኖሚክስ መምህርና ጸሓፊ**

**(ሽክም የበዛበት ትውልድ፡ 2009 እና**

**የምሥራቃዊት ኮከብ፡ 2010 መጻሕፍት አዘጋጅ)**

ማንም ጤነኛ ማስተዋል የቻለ ሰው በቀላሉ እንደሚረዳው ሀገራችን በኹለንተናዊ መንገድ መልካም የሚባል ኹኔታ/ዎች ላይ አይደለችም፡፡ ሀገራችን በኹለንተናዊ አቅጣጫ በጽኑ ታማለች፡፡ ማሳያዎቹ ብዙ ቢኾኑም በዋናነት አኗኗራችን ትልቅ ምስክር ከመኾኑም በላይ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የምንሰማቸው፣ የምናያቸው፣ የስብሰባ ብዛቶች፣ የሚገለጹልን መግለጫዎች፣ የሚታወጁብን አዋጆች፣ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ ማሳሰቢያዎች እና አንዳንድ የሚስተዋሉ የሽኩቻ መታያ ነገሮች ሌሎች ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ኹለንተናዊ ቀውሶች ዛሬ ባጋጣሚ የተከሰቱ ሳይኾኑ በጊዜ ሂደት ትላንት ከትላንት ወዲያ ምቹ ኹኔታን ሲጠብቁ በነበሩ ኹለንተናዊ የውስጥና የውጭ ገፊ ምክንያቶችና ኃይሎች እንደተከሰቱ አያጠራጥርም፡፡

ይህም በመኾኑ የተለያዩ አካላት እንደየግንዛቤያቸውና ፍላጎታቸው ቀውስ ውስጥ የገባንበትን ምክንያት በተለያየ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡፡ ገዥው ፓርቲ የሚሰጠው ምክንያት ተፎካካሪ ኃይሎች ከሚሰጡት ምክንያት የተለየ፤ የፖለቲካ አክቲቪስቶች በሀገር ውስጥም ኾነ በውጭ ያሉ ደግሞ ከራሳቸው እንቅስቃሴ ጋር አስተሳስረው ያስቀምጣሉ፤ የተለያዩ ሥርዓት ለማፍረስ የሚታገሉ ኃይሎች በአንጻሩ እንደትግላቸው ውጤት አድርገው በማስቀመጥ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ይተነትናሉ፡፡ ልዩነታቸው እጅግ የተለያየና እርስ በራሱም እጅጉን የሚቃረንና የሚቀራረን ከመኾኑም በላይ ይህ ልዩነታቸውና መራራቃቸው የሀገራዊ ቀውሱ ትልቅ ማሳያ ምልክት ያስደርጋቸዋል፡፡

በመኾኑም በተደጋጋሚ የተጠቀሱትን ሳይኾን ***ያልተጠቀሱ፣ ትኩረት ያልተሰጣቸውን፣ አጽንዖት ሊሰጣቸው የሚገባና በልዩ ዕይታ መታየት*** ያለባቸውን ሀገራዊ ቀውስ ውስጥ የገባንባቸውን 11 ዋነኛ ነጥቦችና ማሳያዎች በአንድነት የመጽሔት ጽሑፍ (Essay) መኾኑን ታሳቢ በማድረግ ከስፋቱ፣ ከውስብሰብነቱና ከመጠኑ አንጻር እጅግም ሳይረዝም እጅጉንም ሳያጥር እንመልከት፡፡

**አንደኛ፡ ከጊዜና ከወቅቱ ጋር ያለመራመድ ችግር፤**

በ1987 ዓ.ም መኾን ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? ሌላ የተሻለ አማራጭ ነበር ወይስ አልነበረም? አስገዳጅ ኹኔታዎች ይፈቅዱ ነበር ወይስ አይፈቅዱም? መኾን የነበረበት ሳይኾን መኾን የሚችለው እሱ ብቻ ነበር? የሚሉ ትላልቅ እስካኹን በተለያየ አቅጣጫ የሚነሡ ሀሳቦችና ክርክሮቻቸውን እንዳለ አስቀምጠን *<u>ከኾነው</u>* ስንነሣ ሀገራችን - ፌደራላዊ ሥርዓተ መንግሥትን መከተል ጀምራለች።

እያንዳንዱ ሥርዓተ መንግሥት አሃዳዊም ይኹን ፌደራላዊ የየራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ይኖሩታል። ለአብነት፡- አሃዳዊነት ከባቢያዊ ራስን በራስ የማስተዳደር ሂደት ላይ ተጽዕኖ በማሳረፍ ማዕከላዊ መንግሥቱን ያጠናክራል። በሌላ በኩል ፌደራላዊ ደግሞ የማዕከላዊ መንግሥት እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ በማሳረፍ ከባቢያዊነትን ያጠናክራል።

ስለኾነም እንደሀገር የተመረጠውን ሥርዓተ መንግሥት ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመተንተን - ጠንካራውን የማዳበሪያና አሉታዊ ተጽዕኖውን ደግሞ የመቀነሻ አልፎ ተርፎም ወደ ጸጋ የመለወጫ ተግባራት ሊከናወኑ ሲገባ ትርጉም ባለው መንገድ ሳይሰራበት ቆየ።

በተለይ በጊዜ ሂደት ከፍላጎት/ቶች ዕድገት፣ ከዓለም ኹለንተናዊ ኹነቶች መለዋወጥ፣ ከተለያዩ ኃይሎች የጥቅም ትስስርሽና እንቅስቃሴዎች፣ ከሕዝብ ብዛት አንጻር፡ ከፍ ሲል የከባቢያዊነት ኹለንተናዊ እብጠት - የሀገራዊነቱ አደጋ - ዝቅ ሲል ከባቢያዊነቱ ደግሞ ወደ መንደርተኝነት ዝቅ ብሎ የከባቢያዊነቱ አደጋ እንዳይኾን በኹለንተናዊ መንገድ ቀን ከለሊት በኹለንተናዊ መንገድ እንቅልፍ አጥቶ መስራት ሲገባ ቀን ከለሊት በሥርዓት ማፍረስ ሀሴት - ስካር ውስጥ በማንቀላፋት፣ በመቆየት፣ ቆሞ በመቅረትና ጊዜና ወቅቱ ከሚጠይቃቸው ኹለንተናዊ ኹነቶች ጋር እያስተዋሉ ነገሮችን አለማሻሻል ይባስ ብሎ በመጡበት መንገድ ለመቀጠል መሞከር እነኾ ለዛሬ አደረሰን።

**ኹለተኛ፡ የመጡበትን ከመዘንጋት ባሻገር ቆሞ መቅረት፤**

ሥርዓት በማፍረስ ሂደት ከቀጥተኛ የውጊያ ቦታ ራቅ ብለው ለሱ ቀጥተኛ ደጋፊ ስራ ሰርተው ለድል የበቁ ተጠቅልለው ቢሮክራሲ ውስጥ በመግባታቸውና የቢሮክራሲ እስረኛ በመኾናቸው ከሳጥን ውጭ (out of box) እንዳያስቡና ማሰብን ራሱ እንደጠላት እንዲመለከቱ አደረጋቸው።

ሥርዓት በማፍረስ ሂደት እርስ በራስ እጅጉን በመንፈስ ተግባብተው ይሰሩ የነበሩ አካላት የመንፈስ አለመግባባታቸው አደባባይ መውጣት፤ የመጡበትን ዕሴትና ዲሲፕሊን ጊዜና ወቅቱ በሚጠይቀው ዕሴትና ዲሲፕሊን አለመተካት፤ሥርዓት በማፍረስ ሂደት በርዕይና በዓላማ ለመታገልና ለማታገል ባሕል፣ ትምህርት፣ ማንቃትና ማደራጀትን በመጠቀም ለድል ከበቁ በኋላ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል ዕሳቤና አስተምህሮን መሰረት ያደረገ ትርጉም ያለው ትውልድ ተሻጋሪ ርዕይና ዓላማ አለማስቀመጥ በመኾኑም የመጡበትን ቀን ከለሊት ሲለፉበት የነበረውን ባሕልን፣ ትምህርት፣ የማንቃትና የማደራጀት ተግባር በጥራት እጅግ የወረደ እንዲኾን በማድረግ ይህን ደካማነት ይዞ ኹሉን የመቆጣጠር ፍላጎትና ተግባር ዛሬ ላለንበት ኹለንተናዊ ኹኔታ ዳርጎናል።

**ሶስተኛ፡ ሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ አልባነት፤**

ነገሮች በኹለንተናዊ መልኩ መኾን ከሚገባቸውና ከሚችሉት እጅጉን በወረደና በዘቀጠ ደረጃ የምናገኛቸው እንደሀገር ከኹላችን በላይ የኾነ ቀን ከለሊት እንቅልፍ የሚነሣን፤ ኹለንተናዊ ልዩነቶቻችንን መሸከም የሚችል፤ ሳንነጋገር የምንግባባ - ሳንገናኝ የምንተዋወቅ - በመንፈስ የምንተሳሰር ዜጎች ለመኾን የሚያስችል ትርጉም ያለው በዕሳቤ ደረጃ የዳበረ፣ በእምነት የሚገለጽ፣ በእውቀት የሚተነተንና በተግባር የሚረጋገጥ እንደግለሰብ፣ እንደቡድንና ተቋም በኹለንተናዊ መንገድ የምንተጋበት ሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ የለንም፡፡

የነዚህ አለመኖር ከኹሉ በላይ በፖሊሲ/ዎች፣ ስትራቴጂ/ዎች፣ ፕሮግራም/ሞች፣ መመሪያ/ዎች፣ ደንብ/ቦች - - - ላይ እጅግ የተሳሳተ ለየቅል፣ ግራ የተጋባ፣ ተመጋጋቢ ያልኾነና ወጥነት የሌለው የኾነ ተግባራት መበራከት፤ ነገሮችን የምናይበት፣ የምንመዝንበት፣ የምንገመግምበትና የምንስልበትን ዕይታ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

ስለሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ አልባነት በሰፊው በዚሁ መጽሔት የጥቅምት ዕትም የቀረበ ሲኾን አልባነቱ ያስከተለው አለመግባባት፣ አለመደማመጥና በመንፈስ አለመዋሃድ የምንመለከተው ነባራዊ ኹኔታ ላይ ጥሎናል፡፡ እንዲያውም እንደሀገር በማዕቀፍና ርዕይ አልባነት ጉዞ እየተጓዝን እስከ ዛሬ መቆታችን የሚደንቅ ነው፡፡

**አራተኛ፡ ከሥልጣን ፖለቲካ ወደ ፖለቲካ አለመሻገር፤**

ለዘመናት እንደነበረው ሥልጣንን ኹሉን ነገሩ (Power is everything) ከሚያደርግ ወደ ሀገራዊ ማዕቀፍን ኹሉ ነገሩ (National Framework is everthing) ወደ ሚያደርግ ፖለቲካ አለመሻገራችን ዛሬም ኹለንተናዊ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፡፡

በእምነት፣ በእውቀትና በድርጊት ደረጃ እንደግለሰብ፣ ቡድንና ተቋም በሥልጣን ፖለቲካ አስተሳሰብና አመለካከት ቅኝ በመገዛታችን የተነሣ ጠላት የመፈለግ፣ ጠላትነትን (Enemity) የሴራና ትንታኔ መሣሪያ የማድረግ፣ "እኔ አውቅልሃለው!"፣ 'የእኔ መንገድ ብቻ!'፣ 'እኔ ባልኩት ብቻ!'፣ 'ያለኔ ሀገረ ትፈርሳለች!'፣ 'ያለኔ ሌላ መንገድ የለም!'፣ 'ኹሉን ነገር የመቆጣጠር ፍላጎት'፣ ኹሉ ነገር ውስጥ የመግባት ጥረት፣ 'እኔ ያልኩት ካልኾነ ብቻ ሞቼ እገኛለው!' - - - በሚል ጥረት ውስጥ መኖርን ዋነኛ መገለጫችን አድርገን በመቆየታችንና በመዝለቃችን ዛሬ ላለንበት ኹለንተናዊ ኹኔታ ተዳርገናል፡፡

የሥልጣን ፖለቲካ በባሕሪው ጥብቅ (rigid)፣ ወግ አጥባቂነት (conservatism) የሚኀላበት፣ ለለውጥ እጅግ ዘገምተኛ (static behaviours) የሚኾን፣ ከወደፊት ይልቅ ከኃላ ትላንት አንጻር ነገሮችን የሚመለከት /የትላንት ማዕቀፍ ቅኝ ተገዢ/፣ በትንሹ የሚረካ፣ የታሪክ ፍጻሜ ቅኝ ተገዥ /በታሪክ ለመኖር የሚተጋ/፣ የገዥነት /managerial/ ባሕሪያትና ጠባያትን የሚላበስ፣ ትርጉም ያለው ትውልድ ተሻጋሪ ርዕይ፣ ግብና ዓላማ የሌለው፣ በኹኔታዎች የሚመራ ሲኾን ፖለቲካ በአንጻሩ የመሪነት (leadership) ባሕሪያትና ጠባያትን የሚይዝ፣ ከኹኔታዎች ጋር ራሱን መቀየርና ማሻሻል የሚችል (flexible)፣ ለለውጥ ከፍተኛ ፍላጎት (eagerness) ያለው፣ ነገሮችን ከወደፊት አንጻር የሚመለከት፣ በትንሹ የማይረካ፣ ታሪክ ለመስራት የሚተጋ፣ ትርጉም ያለው ትውልድ ተሻጋሪ ርዕይ፣ ግብና ዓላማ የሚኖረው፣ ኹኔታዎችን የሚመራ ነው፡፡

በሌላ በኩል የ'ሥልጣን ፖለቲካ' የራስ አሸናፊነትን ብቻ ሳይኾን የሌላውን ተሸናፊነት ጭምር በተግባር ማረጋገጥ ይሻል፤ ከመኖር ባሻገር የሌላው አለመኖርን፤ ከማግኘት ባሻገር የሌላው አለማግኘትን/ማጣትን፤ ከመበልጸግ ባሻገር የሌላው መደህየትን፤ ከግማሽ ማግኘት ሙሉ ማጣትን፤ ከመቆጣጠር ባሻገር የሌላው ሎሌነትን፤ ከመተባበር ባሻገር የሌላው አለመተባበርን የሚሻ - እንደጦርነት ስልት ራስን ከማጠንከር ባሻገር ሌላውን ማዳከምን የሚይዝ - ሁለት ስለት ያለው ጠላት ፈላጊ እንዲሁም ጠላት 'ፈጣሪ'/አድራጊ ነው። በዚህም የተነሣ መተማመን አልባ ይኾን ዘንድ ግድ በሚልበት ኹኔታ የሚኖርና የሚልበትን ምቹ ኹኔታ በመፍጠሩ አኹን ላለንበት ኹለንተናዊ ቀውስ ተዳርገናል።

**አምስተኛ፡ የሀገራዊ አምዶች በእጅጉ መዘንጋት፤**

በማንኛውም ሀገር የሀገር ግንባታ (Building Nation) እና ሕብረተሰብን የማነጽ (Reshaping Society) ሂደት ትምህርት፣ ባሕልና ታሪክ ታላቅ የማይተካ ሚና ያላቸው ቢኾንም በሀገራችን የትምህርት ጥራት ጉዳይ እጅግ የወረደ አለፍ ሲልም ከአኗኗር ዘይቤያችን ጋር ያልተዋሃደና እኛነታችንን መሰረት ያላደረገ ነው።

ከባሕል አንጻር ሥነ - ጽሑፋዊ ጥበቦች (ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ብሎም ፖለቲካዊ የኾኑ ማንነቶቹ የሚገለጹባቸው ድርሰቶች (ልብ ወለዶችና ኢ. ልቦለዶች)፣ ግጥሞች፣ ተውኔቶች፣ ሥነ ቃሎች፣ መነባንቦች - - - ወዘተ)፤ እይታዊ ጥበቦች (የሥዕል፣ የፎቶ ግራፍ፣ የምልክት ሥራዎች፣ የፊልም፣ የድራማ፣ የጭውውት፣ የኪነ - ህንጻ ሥራዎች፣ የፋሽን፣ የዲዛይን፣ - - - ወዘተ)፤ ትዕይንታዊ ጥበቦች (የሙዚቃ፣ የትያትር፣ የውዝዋዜ፣ የጭፈራ፣ ባሕላዊ የሐዘንና የደስታ መገለጫዎች የኾኑ ተግባራት፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የሃይማኖት በዓላት መገለጫዎች)፤ የዕደ ጥበብ ሞያ (የእንጨትና የቆዳ ሥራ፣ የሸመና ሥራ ፣ የጌጣ ጌጥ ሥራ - - - ወዘተ) ሥራዎችን ከሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ ጋር ባለመስተሳሰራቸውና እንዲስተሳሰሩ ትርጉም ያለው ሥራ ባለመሰራቱ እንደሀገር ሀገራዊ ሕልውናችን እንኳ ሳይቀር በማያሻማ ኹኔታ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገብቶ ይገኛል።

ከታሪክ አንጻር ***የእያንዳንዱ የሀገራችን ክፍል ታሪክ የጋራ ታሪካችን!*** መኾኑን በታሪክ ተግባቦት ላይ አንዱ ከሌላኛው ጋር እንዲተዋወቅና በመተዋወቅ ውስጥ በባለቤትነት ስሜት እንዲይዘው ሥራ መሰራት ሲገባቸው ለተራ አላፊና ዘላቂ ላልኾነ የሥልጣን ፖለቲካ ጥቅም እንዲውል በመደረጉ እንደሀገር ወጥነት ያለው የታሪክ ትምህርትና አስተምህሮት የሌለን አሳዛኝ ዜጎች ከመኾናችንም በላይ እርስ በራሳችን በ21ኛው ክፍለ ዘመን እዚ ቁጭ ብለን አውሮፓውያንና ሰሜን አሜሪካውያንን እንድናውቅ ኹለንተናዊ ስራ ተሰርቶብን ሰለነሱ እየደሰኮርን - እርስ በራሳችን የማንተዋወቅ ኾነን ጭራሽ እንደባዕድ የምሳደድ፣ የምንበራረርና የምንሰዳደብበት ደረጃ ላይ ደረስን። ከድርጊቱ በላይ ድርጊቱ የተሸከመው እምነትና እውቀት፤ ከፈጻሚዎቹ በላይ በመላው የሀገራችን ክፍል የሚገኝ ሕዝብ ዝምታ ብሎም የፈጻሚዎች በበቂና ፍጥነት ባለው መንገድ ለፍርድ አለመቅረብ ያለንበትን ቀውስ ጥልቀት ያሳያል።

ዛሬ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአውሮፓ ስደተኛ ኾነው በአለም አቀፍ ስምምነቶችና ሕጎች ተጠቅመው መብት በሚጠይቁበትና ተጽዕኖ በሚፈጥሩበት ዘመን እኛ ግን እርስ በራስ እንፈነቃቀላለን። ታሪካችንን አለማወቃችንና እንድናውቅ አለመደረጋችን በባለቤትነት ስሜት እንዳንተያይ አደረገን የዚህም ሀገራዊ አምዶች ትርጉም ባለው መንገድ

መረሳት፣ አለመሰራትና አለመታሰባቸው ውጤት በኹለንተናዊ ቀውሶቻችን የሚታይ አንድ ዋነኛ መንሥኤ ኾኗል፡፡

**ስድስተኛ፡ የተቋማዊነት መደነባበር፤**

የመንግሥት አካላት የኾኑት ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ ፈጻሚ አካላት እርስ በራሳቸው የሚደጋገፉ፣ የሚጠባበቁና የሚቆጣጠሩ መኾን አልቻሉም፡፡ ያልኾኑትም መነሻና መዳረሻውን በሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ ላይ መሰረት አድርገው ባለመከፋፈላቸው ነው፡፡

ተቋማዊ አስተሳሰብና አመለካከት በእምነት፣ በእውቀትና በተግባር ደረጃ እንደግለሰብ፣ ቡድንና ተቋም ባለመዳበሩ እነኾ የመንግሥትና ፓርቲ አለመለየት እና የአመራር መተካካትን በተቋማዊ አሰራር ውስጥ በኹለንተናዊ መንገድ ማስፈን እየተቻለ በዘመቻና በአጀንዳ መልክ ቀርቦ ለሥልጣን ፖለቲካ መሣሪያነት በመዋል ሀገርና ትውልድ ዋጋ በመክፈል ላይ ይገኛል፡፡

አመራሮችን በተቋማዊ አሰራር ለአብነት፡- በቆይታ ጊዜና በእድሜ በማስቀመጥ አንድ ሰው ከ25 ዓመታት በላይ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል መኾን አይችልም፡፡ ከ5 ጊዜ በላይ የሥራ አስፈጻሚ አባል መኾን አይችልም፡፡ - - - ወዘተ በሚሉ ከኹሉ በላይ ለኹሉም በሚያገለግሉ ለማንም የሴራ ግልጋሎት የማይውሉ ተግባራትን ማስቀመጥ እየተቻለ በሌላ መንገድ ለቡድናዊነት ተግባር ላይ መዋሉ ዛሬ ላለንበት የውስጥ ሀገራዊ ቀውስ አንዱ ገፊ ምክንያት ኾኗል፡፡

**ሰባተኛ፡ አሳቢ አካል አልባ ሀገር መኾን፤**

እንደሀገር ለግብርና - ግብርና ሚኒስቴር፣ ለጤና - ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለባሕልና ቱሪዝም - ባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር - - - ወዘተ መስሪያ ቤት ሲኖር በሀገራችን ዋነኛ ተግባሩን ስለሀገር ማሰብ ያደረገ - ሀገራችን በኹለንተናዊ ዘርፍ ምን ላይ ነበረች? አኹንስ ምን ላይ ነች? ምን ላይስ መድረስ ትችላለች? የዜጎች የአስተሳሰብና አመለካከት ደረጃ ምን ላይ ነው? በዚህ ሂደት ያሉ ዋነኛ ፈተናዎችና ችግሮች ምንድናቸው? እንዴትስ ማለፍ ይቻላል? አለምና የአለም ሀገራት በዚህ ረገድ ምን እያደረጉ ነው? ከነሱ አንጻር እኛ ምን ላይ ነን? ምን አይነት ተጽዕኖ እያደረሱብን ነው? ለወደፊቱስ ምን ሊያደርሱብን ይችላሉ? ብሎ ከርዕዮተ ዓለምና ርዕዮተ ሀገር በመነሣት በኹለንተናዊ (በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ) አቅጣጫዎች በዕሳቤ ደረጃ ቀን ከለሊት በቁጭት የሚያስብ አንድ ጠንካራ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በላይ የኾነ ሀገራዊ ተቋም አለመኖሩ ዛሬ ላለንበት ኹለንተናዊ ቀውስ ግብዓት ኾኗል፡፡

እንደሀገር በሀገራችን በሀገር ጉዳይ 24 ሰዓት የሚሰራ **ብቸኛው ተቋም የጸጥታ አካሉ ብቻ** ነው፡፡ ስለሀገር ግንባታ (Building Nation) እና ሕብረተሰብን የማነጽ - የመቅረጽ (Reshaping Society) ጉዳይ ዜጋዊ አስተሳሰብና አመለካከትን መነሻውና መዳረሻው አድርጎ የሚያስብ፣ እንቅልፍ የሚያጣ ጠንካራና ተጽዕኖ ፈጣሪ አካል የለንም፡፡ በዚህም የተነሣ የተከሰቱ ብቻ ሳይኾን ሊከሰቱ በሚችሉ ተጨባጭ ኹለንተናዊ ኹኔታዎች ላይ የሚያስብና ሀሳቡን የሚያደራጅ ከቢሮክራሲ እስር ቤት የራቀና ከሲስተም ወጥቶ ስለሀገራዊና ሕዝባዊ

ሲስተም የሚተጋ አካል አለመኖሩና እንዲኖር አለመደረጉ ቀውስ ውስጥ በመክተት ኹለንተናዊ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፡፡

**ስምንተኛ፡ የመሪነት አዘቅጥ መበራከት፤**

እኛ በኢኮኖሚያዊ መለኪያዎች ድሃ የድሃ ድሃ ከሚባሉ ሀገራት መሐከል የምንመደብ ከ106 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያለን ኾነን 20 ቢሊዮን ዶላር እንኳ የማይሞላ አመታዊ በጀት ያለን ከዚህም ውስጥ ቀላል የማይባል ቁጥር ያለውን እርዳታና ብድርን ተስፋ የምናደርግ ኾነን ሳለ በዝቾ እንኳ እርስ በራሳችን የምንበላላና የምንካሰስ መኾናችን እንደተጠበቀ ኾኖ በጀት የሚመልሱ፣ በጀት አጠቃቀማቸው እጅግ የወረደ፣ በበጀት መዝጊያ ወቅት ገንዘብ ተመላሽ ላለማድረግ የሚደረግ ሩጫና ትርምስምስ ያለባቸው በርካታ ተቋማትን ስንመለከትና እንዲህ የገዙና ንዝህላልነታቸውን፣ አቅም አልባነታቸውንና የሀገር ዕዳ መኾናቸውን ለዓመታት ያስመሰከሩ ሰዎችን የተሸከመች ሀገር፤ ከኢትዮጵያ እልፍ አላፍ ችግሮች አንጻር በጀት ሊያንስ እንጂ እንዴት ይመለሳል? እንዲህ መኾን የመሪ አዘቅጥነት አይደል? ይህን የተሸከመች ሀገር ቀውስ ውስጥ ያልገባች ማን ሊገባ?

በርካታ አቅምና ብቃት ኖሯቸው ሥራ አጥተው በሚንከራተቱባት ሀገራችን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሹመኞች፤ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ወሳኝ የሀገሪቱን ኃላፊነት የተሸከሙ ሰዎች እየገዙ የሚማሩባት ሀገር መኾኗ፤ እውን የኢትዮጵያ ችግር እንኳንስ እየተማሩ ሙሉ ጊዜ ሰጥቶ እንኳ ሰጥቶ ቢሰራበት ይቻላል? እውን ለዓመታት መሰብሰብና ሌሎችን መሰብሰብ ሥራቸው ያደረጉ ሰዎች ለመማር ጊዜ አግኝተው መማር ይችላሉ? እውን ሌላው ተምሮ ሥራ በማያገኝባት ሀገር ሌላው እየተማርኩ ልግዛ ማለት ከየት መጥቶ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል? ይህም ሲባል አማራጭ የሌላቸውን ሥርዓት በማፍረስ በትጥቃዊ ትግል ሂደት ተሳትፈው የነበሩትን ሳይኾን ከዚያ በኃላ ሥርዓት በመገንባት ሂደት ያለውን እንደኾነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

በዲግሪና በማስተርስ አካውንቲንግ የሚያስተምሩ ግን ራሳቸው በበጀት አጠቃቀምና ሀብት አያያዝ የዘቀጡ፤ በዲግሪና በማስተርስ ኦዲቲንግ እያስተማሩ ራሳቸው ኦዲት ባለመደረግና በኦዲቲንግ መደነባበር ውስጥ ተዘፍቀው፤ በዲግሪና በማስተርስ በሰላምና ግጭት አፈታት የሚያስተምሩ ነገር ግን ራሳቸው በኔትወርክ፣ በቡድነኝነትና በጥቅማ ጥቅም ተቧድነው በሚፏከቱባትና በሰላም መደፍረስ ግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ የሚኾኑባት፤ የሎጂክ ኮርስ እያስተማሩ በአመክንዮ ሥራዎችን ከመስራት ይልቅ በስሜትና በግምት የይድረስ ይድረስ የሚሰሩ ዩኒቨርስቲዎች በሞሉባት፤ ሀሳብና ዕሳቤን ከተለያየ ዘርፍ አንጻር እያስተማሩ በሀሳብና ዕሳቤ ማዳበር ዙሪያ ለመስራት ከሳጥን ውጭ (out of box) ማሰብና መንቀሳቀስን ነውር ባደረጉ ተቋማት፤ ፕሮጀክት በማስተርስ እያስተማሩ ራሳቸው በውስጣቸው ባለ የፕሮጀክት አፈጻጸም ማፈርያ በኾኑ ህንጻ እንኳ ሳይቀር ጠፉ በሚባልባት ሀገር፤ ማኔጅመንት እያስተማሩ ራሳቸውን ማኔጅ ማድረግ በማይችሉ አካላት የሚመሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተይዞ!!! እውን ሀገራችን አኹን የገባችበት ውጥንቅጥ ቢያንስባት እንጂ የሚበዛባት ናትን? በዚህ ኹኔታ ቀውስ ያልተከሰተ መቼ ሊከሰት?

**ዘጠነኛ፡ የፖለቲከኛ እጦት፤**

እንደሀገር በሀሳብና በዕሳቤ ደረጃ ከሥልጣን ፖለቲካ ወደ ፖለቲካ፤ ከገዥነት ወደ መሪነት ትርጉም ባለው ኹለንተናዊ መንገድ ያሻገረ መሪ - ፖለቲከኛ ማግኘት አልቻልንም። በሀገራችን ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ስትራቴጂስቶች፣ ሀገርን ያጥለቀለቁ ቢሮክራቶች፣ እጅግ የበዙ ካድሬዎች የተንሰራፉባትና ባለሙያዎች የሞሉባት በመኾናችን በተከሰቱ ብቻ ሳይኾን ሊከሰቱ የሚችሉ ኹለንተናዊ ኹነቶችን ተረድቶ አቅጣጫ የሚሰጥ ዘመን ተሻጋሪ መሪ አላገኘንም።

**አስረኛ፡ ቁጭት አልባ ጉዞ፤**

በአንድ ሀገር ኹለንተናዊ የለውጥ ጉዞ ውስጥ ቁጭት ትልቅ መሣሪያ ነው። ቁጭት ሳይፈጥሩ አንዳች ታላቅ ለውጥ ማምጣት እጅግ አዳጋች ነው። በሀገራችን ለቁጥር የሚያታክቱ እልፍ አላፍ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከጾታ፣ ከሀብት፣ ከትምህርት - - - ልዩነቶቻችን በላይ ኹላችንን የሚመለከቱ ኹለንተናዊ ችግሮች አሉብን። ግን ባለፉት 27 ዓመታት እኛ ኢትዮጵያውያን በአንድም <u>ታላቅ ሀገራዊ የውስጥ ችግር</u> ላይ ከኹለንተናዊ ልዩነት/ቶቻችን በላይ ተሰልፈን የታየንበት ተግባር የለንም። የጊዜና የኹኔታዎች ጉዳይ እንጂ ይህ ሳይኖር ቀውስ ውስጥ ከመግባት ይልቅ አለመግባት ያስደንቃል።

**አስራ አንደኛ፡ በብዙ ነገሮች ኃላ የቀረን መኾናችን፤**

ምንም እንኳ እንደሀገር ረዥም ታሪክ ካላቸው ሀገራት መሐከል የምንመደብ ቢኾንም ለፓርቲ ፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ ለውይይት ባሕል (ልዩና ተቃራኒ ሀሳቦችን የማስተናገድ)፣ የዲሞክራሲያዊ ዕሴት፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት፣ የአርቀ አሳቢነት፣ የዕምነት እድገት፣ የተቋማዊነት አስተሳሰብና አመለካከት - - - ባሕል ያላዳበርንና ኃላ ቀር መኾናችን ዛሬ ላለንበት ኹኔታ/ዎች ዳርጎናል።

ጠቅለል ሲል እኛ እኮ ገና! ገና! ገና! የፖለቲካ ኃይሎቻችን በሥርዓተ መንግሥት አይነት ላይ በማዕቀፍ ደረጃ እንኳ ተግባቦት የሌላቸው፤ በሕገ መንግሥቱ ይዘትና አይነት ላይ ልዩነታቸው እጅጉን የሰፋ፤ ሀገራዊ ምንነትና ትርጓሜ ላይ አራንባና ቆቦ የኾኑ፤ ታሪክን ዋነኛ የሥልጣን ፖለቲካ መሣሪያ የሕልውናቸው ማጠንጠኛ ያደረጉ፤ እርስ በራስ በጠላትነት የሚተያዩ፤ ጠላትነትን (Enemity) የሥልጣን ፖለቲካቸው እንቅስቃሴ እስትንፋስ ያደረጉ፤ አብሮ መስራት አይደለም - አብሮ መታየትን እንደወንጀል የሚቆጥሩ፤ በአወቅኩሽ ናቅኩሽ - በሴራና በማስመሰል የተዋጡ፤ በጥቃቅንና አነስተኛ ሀሳቦች የተሞሉ፤ በዕሳቤና በሀሳብ ልዕልና ድርቅ የሚታወቁ፤ ሥልጣን ኹሉ ነገር ተደርጎ በሚታሰብበትና ለዚህም ኹለንተናዊ የውስጥና የውጭ ትግልና ትግሎችን በሚያደርጉባት ሀገር እንዳለን መዘንጋት አይኖርብንም።

በዚህ ውስጥ የነበረች፣ ያለችና የምትኖር ሀገር ደግሞ የኹለንተናዊ ቀውሱ/ሶቹ አይነት፣ መጠን፣ ስፋት፣ ስርጭት፣ ጥራት፣ ተጽዕኖ - - - ወዘተ ይለያይ እንደኾነ እንጂ ከቀውስ/ሶች ተለይታ አታውቅም። ከዚህ ካልወጣችም በቀር ልትለይ ፈጽሞ አትችልም።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ አስራ አንድ ዋነኛ ነጥቦች በተለያዩ አካላት ተደጋግመው ከሚገለጹ መኾን ከሚገባው ይቅር መኾን ከሚችለው ፍትህ፣ ዲሞክራሲ፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ ነጻነት፣ መልካም አስተዳደር፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፣ ምቹ

ምህዳር፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት - - - ወዘተ አንጻር በርካታ ችግሮች በሀገራችን እንደነበሩና እንዳሉ አኹንም ቢኾን ላለንበት ኹለንተናዊ ነባራዊ ኹኔታ የነዚህ አስተዋጽዖ እጅግ ከፍተኛ እንደኾነ ባለመዘንጋት ነው።

የሀገር ኹለንተናዊ ለውጥ **የርቢ ውጤት** ነው። እንኳንስ የተመሳሳይ ኃይሎች ይቅር የተለያዩ ፍጹም ተቃራኒ ኹለንተናዊ ነገሮች ርቢ ውጤት የመኾኑን እውነታ (Reality) ና እውነት (Truth) ባለመዘንጋት ዘመኑ በሚጠይቀው ከኃይልና ሴራ ልዕልና ይልቅ በሀሳብና ዕሳቤ ልዕልና፣ ከከባቢያዊነትና ስሜታዊነት ይልቅ በሀገራዊነትና በምክንያታዊ ዕሳቤ፤ ከታሪክ ፍጻሜ ደስኳሪነት ይልቅ በአርቆ አሳቢነት፤ ከተፈጸሙ ታሪኮች ስካር ውስጥ ከመስመጥ ይልቅ በታሪክ ሰሪነት ቁጭት መኖርን የአኗኗርና የመምራት ዘይቤ የሚያደርግ እምነት፣ እውቀትና ድርጊት እንደግለሰብ፣ ቡድንና ተቋም ማዳበርን የግድ ይላል።

ሀገራችን በቀላሉ ወደ ኹለንተናዊ ቀውስ/ሶች አልገባችምና በቀላሉ ትወጣለች ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። **ውሃ እያሳሳቀ እንደሚወስድ ሥርዓተ መንግሥትም ቀስ እያለ ነው ወደ ኹለንተናዊ ቀውስ/ሶች የሚገባውና** ብዙ መስዋዕትነት አስከፍሏልና ብዙ መስዋዕትነት ማስከፈሉ አይቀሬ ነው።

በመኾኑም ሀገራችንን ከኹለንተናዊ ቀውስ/ሶች ለማውጣት በቅድሚያ በቀውሱ ትክክለኛ ዋነኛ መንሥኤዎች ላይ ከምልክቱ/ቶቹ ባሻገር ትኩረት በማድረግ እነሱ ላይ እንደሀገር ሊኖረን ከሚገባ ሀገራዊ ማዕቀፍና ሀገራዊ ርዕይ ጋር በማስተሳሰር ቁጭት በመፍጠር መንቀሳቀስ ይገባል። ፈጣሪ ሀገራችን **ነጻ ፍቃድን** የኹሉ ነገር **ማዕከል** ወደ ሚያደርግ **የዕሳቤ ሂደት** ትገባ ዘንድ ይርዳን!

(በቀጣይ እንደፈጣሪ ፈቃድ *'ሀገራችንን ከቀውስ እንዴት እናውጣ?'* የሚል እንመለከታለን።)

**ቸር እንሰንብት!**